ብልፅግና ፓርቲ
PROSPERITY PARTY

# የብልጽግና ፓርቲ የኮር አመራር ምልመላ መመሪያ

የካቲት/2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ይዘት


መግቢያ ........................................ 1

**ክፍል አንድ** ........................................ 2

**ጠቅላላ ድንጋጌዎች** ........................................ 2

አንቀጽ አንድ- አጭር ርዕስ ........................................ 2

አንቀጽ ሁለት- ትርጓሜ ........................................ 2

አንቀጽ ሶስት- የጾታ አገላለጽ ........................................ 3

አንቀጽ አራት- የመመሪያው ዓላማ ........................................ 4

አንቀጽ አምስት- የአሰራር መርሆዎች ........................................ 4

አንቀጽ ስድስት- የተፈፃሚነት ወሰን ........................................ 4

**ክፍል ሁለት** ........................................ 5

**የኮር አመራር የምልመላ ሂደት እና የምልመላ መስፈርት** ........................................ 5

አንቀፅ ሰባት- የኮር አመራር የምልመላ ሂደት ........................................ 7

አንቀጽ ስምንት- የኮር አመራር የምልመላ መስፈርት ........................................ 5

**ክፍል ሶስት** ........................................ 8

**የኮር አመራር ምልመላን ስለማደራጀት፤ ስለማጽደቅ እና ስለመከለስ** ........................................ 8

አንቀጽ ዘጠኝ-  የኮር አመራር ምልመላን ስለማፅደቅ ........................................ 8

አንቀጽ አስር- የኮር አመራር ምልመላን መረጃ ስለ ማደራጀት ........................................ 9

አንቀጽ አስራ አንድ- የኮር አመራር መረጃን ስለመከለስ ........................................ 9

አንቀጽ አስራ ሁለት- የኮር አመራር ሆኖ ስለመቆየት ........................................ 9

**ክፍል አራት** ........................................ 10

**የፓርቲ ጽ/ቤቶች በኮር አመራር የምልመላ ስራ ላይ የሚኖራቸው ተግባር እና ኃላፊነት** ........................................ 10

አንቀጽ አስራ ሶስት- የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት ........................................ 10

አንቀጽ አስራ አራት- በየደረጃዉ የሚገኙ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት ........................................ 11

አንቀጽ አስራ አምስት- የተለዩ ኮር አመራሮችን ስለመጠቀም ........................................ Error! Bookmark not defined.

**ክፍል አምስት** ........................................ 11

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች** ........................................ 11

አንቀጽ አስራ ስድስት- ከኮር አመራር ስለመታገድ ........ 11

አንቀጽ አስራ ሰባት- ቅሬታ ስለማቅረብ እና የማስተናገድ ሁኔታ ........ 12

አንቀጽ አስራ ስምንት- መመሪያውን ስለማሻሻል ወይም ስለመቀየር ........ 12

አንቀጽ አስራ ዘጠኝ- የመመሪያው ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ ........ 12

**መግቢያ**

የብልፅግና ፓርቲ በአገራችን ሁለንተናዊ ብልጽግናን የማረጋገጥ ራዕይን እውን ለማድረግ በአስተሳሰባቸው፣ በስነ ምግባራቸው፣ በዕውቀታቸው፣ በክህሎታቸውና በአፈፃፀም ብቃታቸው የላቁ ኮር አመራሮችን ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማፍራት የሚያስችል ሥርዓት መፍጠር እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በወሳኝ የፓርቲና የመንግስት የኃላፊነት መደቦች ላይ ተመድበው ውጤት ማምጣት የሚችሉ እና የተለየ የአመራር ብቃት በሚጠይቁ ተልኮዎች ላይ በመሰማራት የፓርቲው ተጨባጭ አቅም ሊሆኑ የሚችሉ አመራሮችን በመለየት አቅማቸውን መገንባት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በየደረጃው ባለው የፓርቲ ጽህፈት ቤቶችና የመንግስት ተቋማት የሚገኙ የኮር አመራሮችን መረጃ በጥራትና ወጥ በሆነ መንገድ አደራጅቶ በማስቀመጥ፣ አመራሩን ቁልፍ ለሆኑ ተልዕኮዎች ለስምሪት ሲፈለግ መጠቀም አስፈላጊ በመሆኑ፤

የፓርቲያችንን ራዕይ፣ ዕሴቶች፣ ዓላማዎችና ግቦች በአግባቡ የተገነዘቡ፣ ወቅቱ የሚጠይቀውን የአመራር ብቃት የተላበሱና ለሌሎች አመራሮች ተሞክሮአቸውን ማካፈል የሚችሉ ኮር አመራሮችን መለየትና ለተልዕኮ ዝግጁ ማድረግ በማስፈለጉ፣

ኮር አመራሮችን በጥራት ለማፍራትና የአመራር ስምሪታችን የፓርቲውን የአሰራር ስርዓትን የተከተለ እንዲሆን የሚያግዝ በመሆኑ፣

በየደረጃው ካሉ አመራሮቻችን በንድፈ ሀሳብ የተሻሉ፣ የጠራ አመለካከትና ጥሩ ስነ ምግባር ያላቸው፤ ተጨባጭ ውጤት ያስመዘገቡ፤ በአባላትና በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው፤ በሚሰጡት አመራርነት ምሳሌ የሆኑ፤ አቅም፣ ብቃት እና ተነሳሽነት ያላቸው፤ በአመራር ምዘና ውጤት ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ ነጥብ ያስመዘገቡና ግንባር ቀደም የሆኑትን ኮር አመራሮችን በመስፈርት በመመልመል ጠንካራ ፓርቲ ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ በመሆኑ፣

ተቋማዊ መሠረት ያለው ከማንኛውም አድሏዊ አሠራር ነፃ የሆነ ግልጽና ውጤታማ የኮር አመራር ምልመላ ሥርዓት መዘርጋት ለእምርታዊ እድገት ቀጣይነትን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 42 መሰረት የኮር አመራር ምልመላ ለማካሄድ ያስችል ዘንድ ይህ የኮር አመራር ምልመላ መመሪያ ተዘጋጅቷል።

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ አንድ- አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "**የብልጽግና ፓርቲ የኮር አመራር ምልመላ መመሪያ**" ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

## አንቀጽ ሁለት- ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1. "**ክልል**" ማለት በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል ፣
2. "**ዞን**" ማለት ለክልል ተጠሪ የሆኑ የዞን አስተዳደሮች፣ የአዲስ አበባ ክፍለ ከተሞች እና በዞን ደረጃ ያሉ ከተሞችን እና ልዩ ወረዳዎችን የሚያጠቃልል ነው፣
3. "**ወረዳ**" ማለት በክልሎች፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በድሬዳዋ አስተዳደር የወረዳ ደረጃ የተሰጣቸው የአስተዳደር አካላትን ያጠቃልላል፣
4. "**አስተባባሪ ኮሚቴ**" ማለት የፓርቲና የመንግስት ሥራዎችን አቀናጅቶ በበላይነት የሚያስተባብር እና በፓርቲው የበላይ አካላት የሚተላለፉ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ተግባር ላይ መዋላቸውን የሚያረጋግጥ በየደረጃው የሚገኝ የፓርቲው አደረጃጀት ነው፣
5. "**የፓርቲ አመራር ኮሚቴ**" ማለት በፓርቲ ዋና ጽ/ቤት እና በየደረጃው በብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የፓርቲ ስራዎችን አቀናጅቶ የሚመራ፣ የሚያስፈጽምና የሚፈጽም የአመራር ኮሚቴ ማለት ነው፣
6. "**አመራር**" ማለት የብልጽግና ፓርቲ አባል የሆኑ እና በፓርቲዉ አማካኝነት በመንግስት መስሪያ ቤቶች፤ በየደረጃው ባለው የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች እና በልዩ ልዩ የአመራርነት ቦታዎች በሹመት፣ በምደባ ወይም ኃላፊነት የተሰጠዉ የፓርቲዉ አባል ነው፣

7. **"አባል"** ማለት የብልፅግና ፓርቲን መተዳደሪያ ደንብ እና ፕሮግራምን ተቀብሎ የአባልነት መብትና ግዴታውን የሚወጣ የፓርቲዉ አባል ማለት ነዉ፣
8. "**ዕጩ ኮር አመራር"** ማለት ለኮር አመራር በዕጩነት ቀርቦ ያልጸደቀለት አመራር ማለት ነው፣
9. **"ኮር አመራር"** ማለት በየደረጃው ባሉ በመንግስት ተቋማት፣ የፓርቲ ጽህፈት ቤቶች እና በልዩ ልዩ የአመራርነት ቦታዎች በሹመት ወይም በምደባ በማገልገል ላይ ከሚገኙ አመራሮች የጠራ አመለካከትና እውቀት ያላቸው፣ ጥሩ ስነ ምግባር ያላቸው፤ በተግባር አፈፃፀም ተጨባጭ ውጤት ያስመዘገቡ፤ በሚሰጡት አመራርነት ምሳሌ የሆኑ፤ የአቅም፣ ብቃት እና ተነሳሽነት ያላቸው፤ በአመራር ምዘና ውጤት ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ ነጥብ ያስመዘገቡ እና ግንባር ቀደም የሆኑ አመራሮች ማለት ነዉ፣
10. **"የአመራር ምዘና ዉጤት"** ማለት አንድ አመራር በፓርቲው የምዘና መመሪያ መሠረት በመደበኛ ስራዎችና በውስጠ ፓርቲ ተልዕኮ አፈፃፀም ምዘና ያገኘው ውጤት ማለት ነው፣
11. **"መርህ አልባ ግንኙነት"** ማለት አንድ አመራር የግል ጥቅም ለማግኘት ወይም ሌላውን ለመጥቀም ወይም ሌላ እኩይ ዓላማን ለማሳካት ሲል ከፓርቲ መርሆዎችና ዕሴቶች ውጭ በሆነና ሕዝብን፣ ሀገርንና ፓርቲን በሚጎዳ መንገድ ከሌሎች አካላት ጋር የሚያደርጋቸውን ግንኙነቶች የሚያጠቃልል ነው፣
12. **"መልካም የፓርቲ ሥነ-ምግባር"** ማለት በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የተደነገጉ የአባልነት ግዴታዎች፣ የፓርቲው መርሆዎች፣ ዕሴቶችና አሰራሮችን ማክበርና በጥብቅ ዲሲፕሊን መፈፀም እንዲሁም ህብረተሰቡ የሚስማማባቸውን የግብረ-ገብ ዕሴቶችን ማክበርና መልካም ተግባራትን በመፈጸም አርአያ ሆኖ መገኘት ማለት ነው፣
13. **"የአፈፃፀም ብቃት ሰባ ፐርሰንት (70%)"** ማለት በመደበኛ ስራዎች የአፈጻጸም ሰባ ፐርሰንት (70%) እና ከውስጠ ፓርቲ ምዘና ሠላሣ ፐርሰንት (30%) ያገኘው ውጤት ተደምሮ ወደ ሰባ ፐርሰንት (70%) ተቀይሮ የሚገኝ ውጤት ነው።

## አንቀጽ ሶስት- የጾታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጹት ሃሳቦች በሙሉ የሴትንም ፆታ ያካትታል።

## አንቀጽ አራት- የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ አላማ ግልፅ፣ አሳታፊና ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት የመፈፀም ብቃት ያላቸው ኮር አመራሮችን በጥራት በመመልመል እና አቅም በመገንባት የፓርቲን አመራር ማጠናከር ነዉ፡፡

## አንቀጽ አምስት- የአሰራር መርሆዎች

የኮር አመራር ምልመላ በሚከተሉት መርሆዎች የሚመራ ይሆናል፡፡

1. የኮር አመራር ምልመላ ሥራ እውነተኛ መረጃ እና ማስረጃን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፣
2. የኮር አመራር ምልመላ ስራ አሳታፊ፣ አካታች፣ ከወገንተኝነት እና አድሎዓዊነት ነፃ መሆን ይኖርበታል፣
3. የምልመላ ሂደቱ በመፈፀም ብቃት ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ የሴቶች፣ ወጣቶች፣ ምሁራን እና የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል፣
4. የኮር አመራር ምልመላ በየደረጃው ሲከናወን በግልጽ አሰራርን የተከተለ መሆን ይኖርበታል፡፡ አሰራርን ያልተከተለ የኮር አመራሮች ልየታ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡
5. የኮር አመራር ምልመላ ሥራ ዕውቀትን፣ ክህሎትን ፣ስነ-ምግባርን እና የተግባር ውጤታማነትን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፣
6. የኮር አመራር ምልመላ ሥራ ጥራቱን የጠበቀ፣ መፃኢ የፓርቲያችንን ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ እና ለሚፈለገው ዓላማ ተደራሽ መሆን ይኖርበታል፣
7. የኮር አመራር ምልመላ ስራ በአመራር ሥርዓታችን፣ በብቃት እና በህብረ-ብሔራዊነት መካከል ሚዛን ለማስጠበቅ የሚያስችል ሊሆን ይገባል፣

## አንቀጽ ስድስት- የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በየደረጃው ባሉ የመንግስትና የፓርቲ መዋቅራዊ አደረጃጀቶች ማለትም ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ በተለያዩ የአመራርነት እርከን ተመድበው ወይም ተሹመው በመስራት ላይ የሚገኙ የብልፅግና ፓርቲ አባል የሆኑ አመራሮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኮር አመራር የምልመላ መስፈርት እና የምልመላ ሂደት

## አንቀጽ ሰባት- የኮር አመራር የምልመላ መስፈርት

ኮር አመራር ሆኖ የሚመለመል አመራር ቀጥሎ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡

1. **የአፈፃፀም ብቃት ሰባ ፐርሰንት** (70%)
   - ሀ) ኮር አመራር ሆኖ የሚመለመል አመራር በሁለት ተከታታይ የአመራር ምዘና አፈፃፀም ውጤቱ በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ ነጥብ ያገኘ መሆን አለበት፣
   - ለ) የሚመራውን ተቋም የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ፣ ከፓርቲ እና ከመንግስት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና የ10 ዓመት መሪ እቅዶች ጋር አጣጥሞ ማቀድና መፈፀም የሚችል፣
   - ሐ) የእቅድ አፈፃፀሙን በተከታታይ የሚገመግም፣ ተግባር ተኮር ድጋፍና ክትትል የሚያደርግና ግብረ መልስ የሚሰጥ፣
   - መ) በተቋሙ በዕቅድ የተያዙ ተግባራትን አውቆ በመፈፀም የላቀ የአፈፃፀም ውጤት ያስመዘገበ፣
   - ሠ) የተሰጠውን ተልዕኮ በተነሳሽነት፣ በቁርጠኝነት እና በውጤታማነት የሚተገብር እና ለተግባራዊነቱ የሚተጋና የሚያተጋ፣
   - ረ) ሥራውን በአሳታፊነት ሃይል የሚያሰባስብና በተደራጀ አግባብ የሚፈፅም፣
   - ሰ) በየጊዜው ሀሳብ የሚያፈልቅ፣ በአዳዲስ ውጤት የታጀበና ተጨማሪ አቅም እየፈጠረ የሚሄድ፣
   - ሸ) ለፈተናዎች የማይንበረከክ፣ የዓላማ ፅናት ያለው፣ የተልዕኮ አፈፃፀም ሳንካዎችን ለይቶ ማሸነፍ የሚችል እና ፈተናን ወደ ዕድል የመቀየር ተሰጥኦን የተጎናፀፈ፣
   - ቀ) የፓርቲውን ዕሴቶችና መርሆዎችን የሚያከብርና የሚያስከብር ፣
2. **ጠንካራ ዕውቀትና ክህሎት ያለው** (30%)
   - ሀ) በፓርቲው መሰረታዊ ዕሳቤዎች፣ አስተምህሮዎች እና መመሪያዎች ላይ ኮር አመራሮችን ለመለየት በማዕከል ተዘጋጅቶ የሚሰጠውን ፈተና ከ25 እና ከዛ በላይ ነጥብ በማምጣት ያለፈ፣

ለ) በብልፅግና ፓርቲ በመደመር ዕሳቤ፣ በፓርቲው ፕሮግራም፣ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ መተዳደሪያ ደንብ እና የአሠራር መመሪያዎች ላይ በቂ ግንዛቤ ያለው እና ከልቡ ያመነበት፣

ሐ) ፈተናው አመራሩ በመረጠው የፓርቲው የስራ ቋንቋ ተዘጋጅቶ የሚሰጠው ይሆናል፣

3. **ስነ-ምግባር (ማለፍ/መውደቅ)**

ሀ) ከሌብነት እና ከብልሹ አሰራር የፀዳ፣

ለ) የሚመራው ተቋም ከሌብነት እና ከብልሹ አሰራር እንዲፀዳ ትግል የሚያደርግ፣

ሐ) የፓርቲውንና የመንግስትን ሚስጥር የሚጠብቅ፣

መ) ፓርቲው የሚሰጠውን ተልዕኮ በእምነት ተቀብሎ ውስጣዊ አቅሙን አሟጦ ተግባራዊ የሚያደርግ፣

ሠ) የውሸት ሪፖርት የማያስተላልፍ እና ለትክክለኛነቱ የሚተጋና የሚታገል፣

ረ) የተቋሙን የአሰራር ሥርዓት በጠንካራ ዲሲፕሊን የሚተገብር እና እንዲተገበሩ ብቃት ያለው አመራር የሚሰጥ፣

ሰ) የተቋሙን ሀብት እና ንብረት ለታለመለት ዓላማ ብቻ የሚያውል እና እንዲውል የሚያደርግ፣

ሸ) ከላይ የተገለፁት (ከ "ሀ-ሰ") ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው ፓርቲው ሌሎች ለዚህ ምዘና አጋዥ የሆኑ ተቋማትን ለመጠቀም በሚስጥራዊነት አመራሩ ያለውን ስነ-ምግባር ያጣራል፣

4. **በኮር አመራርነት ስለመያዝ**

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገለፁት መስፈርቶች (የአፈፃፀም ብቃት፣ ዕውቀት እና ክህሎት) ውጤት ተደምሮ አመራሩ የሚያገኘው ውጤት 85% እና ከ 85% በላይ ከሆነ በኮር አመራርነት ይያዛል፣

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ "ሀ" ላይ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ 3 የተመላከተው የስነ-ምግባር መስፈርትን ያላሟላ አመራር ወይም በስነ-ምግባር ውጤት የወደቀ አመራር በኮር አመራርነት አይያዝም፣

ሐ) በኮር አመራር የተያዘው አንድ አመራር ውጤቱን አስጠብቆ እስከ ቆየ ድረስ በኮር አመራርነት ምደባ እስኪያገኝ ድረስ እንደተያዘ ይቆያል፣

## 5. በአመራር ምዘና ያገኘው ውጤት

ከላይ የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ለአመራር ምዘና ማስፈጸሚያ በተዘጋጀው መመሪያ ቁጥር 10/2015 መሠረት በሚካሄደው የአመራር ምዘና አጠቃላይ ውጤቱ በሁለት ተከታታይ ምዘናዎች በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ ውጤት ያገኘ አመራር መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡ ፡

## አንቀፅ ስምንት- የኮር አመራር የምልመላ ሂደት

1. በየደረጃዉ ባሉ አደረጃጀቶች በተልዕኮ እና በእቅድ አፈፃፀም ዉጤታማነታቸዉ፣ ለፓርቲያቸዉ ባላቸዉ እምነትና ቁርጠኝነትን መሰረት በማድረግ ኮር አመራሮች እንዲመለመሉ ይደረጋል፣
2. የኮር አመራር ምልመላ በዓመት አንድ ጊዜ ሆኖ የሁለት ጊዜ የአመራር ተከታታይ ምዘናን ተከትሎ ባለው አንድ ወር ውስጥ ይከናወናል፣
3. ከዓመት አጋማሽ የአመራር ምዘና በኋላ ወደ አመራርነት የገባ በተከታታይ ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ ውጤት ካመጣ ይያዝለታል፣
4. ለኮር አመራርነት የሚመለመሉ አመራሮች የተቀመጠውን የምልመላ መስፈርት ሙሉ በሙሉ የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፣
5. ለኮር አመራር የሚመለመሉ አመራሮች በአመራር የምዘና ውጤታቸው በተከታታይ ለሁለት ጊዜ ከፍተኛ እና በጣም ከፍተኛ ነጥብ ያገኙ አመራሮች ብቻ ናቸው፣
6. በእጩነት የተያዙት አመራሮች በፓርቲው በዋና ጽ/ቤት በሚዘጋጀው ፈተና ተገቢውን የማለፊያ ውጤት ማምጣት ይጠበቅባቸዋል፣
7. በፈተናው ተገቢውን ውጤት ያስመዘገቡ ዕጩ ኮር አመራሮች ያላቸው ስነ-ምግባር በሚመለከተው አካል እንዲጣራ ይደረጋል፣
8. የስነ-ምግባር ማጣራት ሂደቱን ያለፉ ዕጩ ኮር አመራሮች መረጃቸው ተደራጅቶ እንዲጸድቅ ይደረጋል፣
9. የተቀመጠውን መስፈርት መሰረት በማድረግ ለኮር አመራርነት ብቁ ሆነው ከወረዳ፣ ከተማ እና ከዞን አመራር ፑል የተመለመሉ አመራሮች መረጃቸው በፓርቲው ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አስተባባሪ ኮሚቴ እንዲጸድቅ ይደረጋል፣

10. ከፌደራል እና ከክልል የአመራር መዋቅር ውሰጥ የኮር አመራር ምልመላ መስፈርቱን አሟልተው የተመለመሉ አመራሮች መረጃ በፓርቲው በዋና ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ እንዲጸድቅ ይደረጋል፣
11. የጸደቁ የኮር አመራሮች መረጃ በፓርቲው ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች እና በፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት መረጃ ቋት ውስጥ እንዲደራጁ ይደረጋል።

6. **ሌሎች የፓርቲ ግዴታዎች**

ሀ) የአባልነትና የአመራር ግዴታውን ለመወጣት የግሉን እና የቡድኑን ዕቅድ በብቃት አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደረገ፣

ለ) የአባልነት መዋጮን ጊዜውን ጠብቆ የሚከፍል እና ሌሎች እንዲከፍሉ የሚያደርግ፤

ሐ) ለኮር የተያዘው አመራር ባለበት በተደራጀበት አደረጃጀት (የብልፅግና ቤተሰብና ህብረት) ስብሰባዎች የሚሳተፍ እና ለአደረጃጀቱ መጠናከር የጎላ አስተዋጽኦ የሚያበረክት፣

መ) የፓርቲውን የውስጥ አሰራር ከሚጎዱ ዕሳቤዎች እና ድርጊቶች የፀዳ፣

ሠ) ለፓርቲው እና ለሚመራው ተቋም ግብዓት የሚሆኑ አዳዲስ አስተሳሰቦችን አደራጅቶ የሚያቀርብ፣

ረ) የፓርቲውን ማህበራዊ መሰረት ለማስፋት በተግባራቸዉ ዉጤታማ የሆኑ አዳዲስ አባላትን የሚያፈራ፣

ሰ) በተመደበበት ተቋም የአባላት እና አመራርን አንድነት፣ ነፃነት እና ቁርጠኝነት ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ ተከታታይ ድጋፍ እና ክትትል የሚያደርግ።

# ክፍል ሶስት

## ኮር አመራር ምልመላን ስለማደራጀት፣ ስለማጽደቅ እና ስለመከለስ

### አንቀጽ ዘጠኝ- የኮር አመራር ምልመላ ስለማፅደቅ

1. በወረዳና በዞን ደረጃ የተመለመሉ ኮር አመራሮች መረጃ በክልል የፓርቲ አመራር ኮሚቴ ተደራጅቶ በክልሉ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚጸድቅ ይሆናል።
2. በክልልና ፌዴራል ደረጃ የተመለመሉ ኮር አመራሮች መረጃ በዋና ጽ/ቤት የፓርቲ አመራር ኮሚቴ ታይቶ የሚጸድቅ ይሆናል።

## አንቀጽ አስር- የኮር አመራር ምልመላ መረጃን ማደራጀት

በየደረጃዉ የተመለመሉ ኮር አመራሮች መረጃቸዉ በፓርቲው ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች እና በፓርቲዉ ዋና ጽህፈት ቤት  የአመራር መረጃ ቋት ዉስጥ የሚደራጅ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ አስራ አንድ- የኮር አመራር መረጃን ስለመከለስ

1. በየደረጃው የተደራጀው የኮር አመራር መረጃ ተደራሽ፤ ወቅታዊ እና ተአማኒ እንዲሆን በዓመት ሁለት ጊዜ መከለስ ይኖርበታል፡፡
2. በኮር አመራርነት የተመለመለ አመራር በተከታታይ ምዘና ውጤት ኮር ሆኖ መቀጠል ካልቻለ ከኮር አመራርነት ሊወርድ፣ ከምልመላ ቋትም ሊወጣ ይችላል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሁለት- ኮር አመራር ሆኖ ስለመቆየት

1. ኮር አመራር ከተመለመለበት ጊዜ ጀምሮ በሚሰጠዉ ተዕልኮ ውጤታማነት፣ በዚህ መመሪያ በተቀመጡ መስፈርቶችን በሙሉ ማሟላት መቻል አለበት፣
2. አንድ ኮር አመራር በሁለት ተከታታይ የአመራር ምዘና ተመሳሳይ ወይም ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ ካልቻለ ከኮር አመራርነት ይሰረዛል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሶስት- የተለዩ ኮር አመራሮችን ስለመጠቀም

1. የተመለመለውን ኮር አመራር በሁሉም እርከን ፓርቲ ያለውን የሰው ሃይል አቅምና ተነሳሽነት አውቆ ለተልዕኮ ዝግጁ ለማድረግ ይጠቀምበታል፣
2. በምዘና፣ በተግባር አፈጻጸም፣ በስነ-ምግባር እንዲሁም በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋ የአመራር ጉድለት ሲያጋጥም በጥንቃቄ አመራር ለመተካት ጥቅም ላይ ይውላል፣
3. ከአሰራር ውጭ በተለምዶ አመራር የመተካት ሂደቶች እንዲቀሩ እና ፓርቲው የጠንካራ አመራር ስብስብ እንዲሆን በማድረግ ውጤታማነቱን ለማሳደግ ያግዛል፣
4. የኮር አመራር ምደባው በአመራር ምደባ መመሪያ መሰረት የሚከናወን ይሆናል፣
5. ኮር አመራር የመመልመል ሂደት በአመራር ቋት ከተያዙት መካከል በአመራር ምደባ በተቀመጠው መመሪያ መሰረት በየደረጃው ባለው አስተባባሪ ኮሚቴ ታይቶ አንድ ደረጃ ከፍ ባለው አስተባባሪ ኮሚቴ እየተወሰነ የሚተካ ይሆናል፣
6. በኮር አመራር ፑል ካልተያዘ በስተቀር ወይም በልዩ ሁኔታ ከሙያ ጋር ተያይዞ የሚሾም ወይም የሚመደብ  አመራር ካልሆነ በስተቀር ከኮር አመራር ቋት ውጭ በተለምዶ መመደብ ክልክል ነው፣

7. በተለያዩ ምክንያቶች የኮር አመራር በሚያስፈልግበት ወቅት በኮር አመራርነት የተመለመሉ ሴት እና ወጣት አመራሮች ቅድሚያ እንዲያገኙ ይደረጋል።

# ክፍል አራት

# የፓርቲ ጽ/ቤቶች በኮር አመራር ምልመላ ስራ ላይ የሚኖራቸው ተግባር እና ኃላፊነት

## አንቀጽ አስራ አራት- የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

1. የክልልና የፌዴራል ኮር አመራር ሂደት በማደራጀት እንዲጸድቅ ያደርጋል፣
2. በክልልና በፌዴራል ደረጃ የተለዩ ኮር አመራሮችን በተመለከተ በየጊዜው ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣
3. በየጊዜው ምዘናን ተከትሎ ለዕጩ ኮርነት ለተመለመሉ አመራሮች የሚመጥን የብቃት ምዘናን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊ በማድረግ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣
4. በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ፣ ከነባሩ የመረጃ ቋት ጋር የተቀናጀ ኮር የአመራር መረጃ ቋት እንዲለማ ያደርጋል፣
5. ለፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች በኮር አመራር ምልመላ ዓላማ፣ አፈጻጸም ሂደት ላይ ስልጠና ይሰጣል፤
6. ለፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች አመራርና ባለሙያዎች የመረጃ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስልጠና ይሰጣል ፣ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን በቴክኖሎጂ ግብአት ያበለፅጋል፣
7. ለፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል ፣ግብረ መልስ ይሰጣል፣
8. በኮር አመራርነት የተመለመሉ አመራሮችን የማስፈፀም አቅማቸውን እና ብቃታቸውን የማሳደግ ሥራ ይሠራል፣
9. ከፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች የሚላከዉን የኮር አመርራሮች መረጃ ያጣራል፤ በአግባቡ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል ለታለመለት ዓላማ ይጠቀማል(ያውላል)፤

**አንቀጽ አስራ አምስት- በየደረጃዉ የሚገኙ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት**

1. በየደረጃዉ ለሚገኙ የፓርቲ አመራሮች የኮር አመራር ምልመላ ዓላማ እና አፈጻጸም ሂደት ላይ በየጊዜዉ ግንዛቤ ይፈጥራሉ፣
2. ከክልሉ የፓርቲና የመንግስት መዋቅር የተመለመሉ የኮር አመራሮች ምልመላን በመስፈርቱ መሰረት ያካሄዳሉ፣ ይከታተላሉ፣ ይደግፋሉ፣ ይገመግማሉ፣ ግብረ-መልስ ይሰጣሉ፣ ትክለኛነቱን ያረጋግጣሉ፤ ለክልል አስተባባሪ ኮሚቴ በማቅረብ ያጸድቃሉ::
3. የኮር አመራር ምልመላ በተቀመጠዉ የጊዜ ሠሌዳ መሠረት እንዲካሄድ ያደርጋሉ::
4. የተመለመሉ ኮር አመራሮችን በኮር አመራር ቋት ውስጥ ያደራጃሉ፣ ለፓርቲ ዋና ጽ/ቤት በሪፖርት ያሳዉቃሉ፤
5. የተመለመሉ ኮር አመራሮችን ተልዕኮ ሰጥቶ ያሰማራሉ፤ ይከታተላሉ፤ ይደግፋሉ፤ ይገመግማሉ፤ ይመዝናሉ፣
6. በኮር አመራርነት የተመለመሉ አመራሮችን የማስፈፀም አቅማቸውን እና ብቃታቸውን የማሳደግ ሥራ ይሠራሉ::

# ክፍል አምስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ አስራ ስድስት- ከኮር አመራርነት ስለመታገድ**

1. በአፈፃፀም ድክመት፤ በዲሲፕሊን ግድፈት፤ በብልሹ አሰራር እና በሰርጎ ገብነት የተገመገመ ኮር አመራር ከኮር አመራር ቋት የሚታገድ ይሆናል፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ላይ የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ አንድ ኮር አመራር በራሱ ፍቃድ ከኮር አመራርነት ቋት ሊወጣ ይችላል፣
3. ኮር አመራሮች ለኮር አመራርነት ያበቃቸውን መስፈርቶች በቀጣይ ሳያሟሉና ሳይፈጽሙ ቀርተው፣ የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ፣ ዕሴቶች፣ መርሆዎች መጣሳቸው እና የዲሲፕሊን ግድፈት ፈጽመዉ መገኘታቸው በየደረጃው ባሉ አደረጃጀቶች ከተረጋገጠ ከኮር አመራርነት የሚሰረዙ ይሆናል::

**አንቀጽ አስራ ሰባት፡- ተጠያቂነት የሚያስከትሉ ነጥቦች**

1. የኮር አመራር ምልመላ እንዳይሳካ ሆነ ብሎ ችግር የሚፈጥር በአመራርና አባላት ስነ-ምግባር መመሪያ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፣
2. የሚሰጠውን ፈተና ያለ አግባብ ለማለፍ የሚደረግ እንቅስቃሴ ፈጽሞ ክልክል ነው፡፡
3. ሰርቶ ባገኘው ውጤት ሳይሆን ያለአግባብ በሌላ አመራር ድጋፊ ውጤት እንዲያገኝ ለማገዝ የሚደረግ እንቅስቃሴ ሁለቱንም ተጠያቂ ያደርጋል፣
4. የኮር አመራር መስፈርቱን ሳያሟላና ሂደቱን ሳይጠብቅ የተደረገ ምልመላ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሰባት- ቅሬታ ስለማቅረብ እና የማስተናገድ ሁኔታ

በየደረጃው በሚካሄደው የኮር አመራር ምልመላ ላይ ቅሬታ ያላቸው አመራሮች በብልጽግና ፓርቲ የአመራርና የአባላት የዲሲፕሊን መመሪያ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት መሰረት ቅሬታቸውን በማቅረብ መስተናገድ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ አስራ ስምንት- መመሪያውን ስለማሻሻል ወይም ስለመቀየር

ይህን መመሪያ በማንኛውም ጊዜ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የብልጽግና ፓርቲ ምክር ቤት ሊያሻሽለው ወይም ሊቀይረው ይችላል፡፡

## አንቀጽ አስራ ዘጠኝ- የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ በብልጽግና ፓርቲ ምክር ቤት ከጸደቀበት ከየካቲት/2016 ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**ዐብይ አህመድ(ዶ/ር)**

**የብልፅግና ፓርቲ ፕሬዚዳንት**

**የካቲት/2016 ዓ.ም**